# የምዕራቱ  የምሥራች

ቅፅ 69 ቁጥር 4(820) «በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደጉድፍ እቆጥራለሁ ÷ እርሱንና የትንሳኤውን ኃይል እንዳውቅ በመከራውም እንድካፈል ወደሙታን ትንሳኤ ልደርስ ቢሆንልኝ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ» (ፊል 3÷9-11)

# ለጌታ ዳግም ምፅአት ዝግጁ ናችሁን?

«ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑ÷ የሰው ልጅ በማታስቡት ሰዓት ይመጣልና» (ማቴ 24÷44)

## እኔ ዝግጁ ነኝን?

የእኔ ዝግጁ መሆን ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት በቀጣይነት መዘጋጀቴ ነው። አንዳንዶቹ አሁን ዝግጁ አይደለሁም፤ ነገር ግን ጊዜው ሣይረፍድ መዘጋጀት እችላለሁ ይላሉ። ለክርስቲያን ተገቢው ነገር ሁልጊዜ ለጌታ ምጽአት መዘጋጀት ነው። ክርስቶስ አንዳች የስንፍና ንግግር ተናግሮ አያውቅም፤ እርሱ ደግሞ የቤተክርስቲያን ራስ ነው። (ኤፌሶን 5÷23) የእርሱን ምጽአት ስንጠብቅም የሚጐድልብን አንዳች ነገር የለም (1 ቆሮንቶስ 1÷7) በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ሊኖር የሚገባው እራሱ አምላክም፤ ሰውም የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው። በእኛና በእግዚአብሔር መካከል ትንሽ ይሁን ትልቅ ጉዳይ ጣልቃ ሊገባ አይገባም። መላእክት ይሁኑ ቅድስት ማርያም ወይንም ሌሎች ሰዎችና ፃድቃን በጭራሽ ጣልቃ ሊገቡ አይችሉም።

አሁን ባለንበት ሁኔታ የሐገራችን ኢትዮጵያ ፖለቲካ ይሁን ኢኮኖሚ፤ የዓለም ሰላምና ሌሎች አሳሳቢ ጉዳዮች ሁሉ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚያሳስቡን ሊሆኑ ይገባል። በምናያቸውን በምንሰማቸው ነገሮች በብዙ ጉዳዮች በሀገራችን ኢትዮጵያ ሲሆን ወይንም በኃያላን መንግስታት ተስፋችንን ብንቆርጥም በኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለዘለዓለም ተስፋ አንቆርጥም፤ ክርስቶስ ብቻ አስተማማኝ ተስፋችን ነውና።

## ልባችን ሲፈርድብን እናስተውል

ልባችሁ እየፈረደባችሁ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ በየጊዜው ሲቀሰቅሳችሁ እራሳችሁን ለጸሎትና ለጾም እያዘጋጃችሁ የጌታን ዳግም ምጽአት መጠባበቃን በፅኑ ተያያዙት። (1 ዮሐንስ 3÷19)

ጌታ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ብሎ በቅዱስ ቃሉ የሚያሳስበን ለእርሱ ዳግም ምጽአት መጋጀቱ እጅግ በጣም ተፈላጊ ነገር በመሆኑ ነው።

በክርስቶስ ፀጋ ለማደግ የዚህ ክፉ ዓለም እና የስጋችንን ክፉ ምኞት ለማሸነፍ የሠይጣንን መሰናክልም በመሰባበር የድል ሕይወት የሚኖረን ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሁሌ ተዘጋጅተን ሳንገኝ ስንቀር ነው። (ገላትያ 5÷16& 1ዮሐንስ 3÷2፤ ሮሜ 8÷1)

ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልጵስዮስ 3÷14 ላይ እንዳሳሰበን ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት እርሱን እንድንመስል እንፍጠን። እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ስለሆነ በልባችን ያለውን ነገር ሁሉ ጌታ ስለሚያውቅ ድካማችንን ለእርሱ እያስታወቅን በንስኃ እንዘጋጅ።

እያንዳንዳችን ያለብንን ጉድለት ለጌታ በጸሎት አስታውቀን እንስተካከል። እየሰረቅን አትስረቁ፤ እያመነዘርን አታመንዝሩ፤ እየዋሸን አትዋሹ ማለት አንችልምና። (ማቴዎስ 7÷5)

«አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያም በኋላ ከወድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ»

## እንዴት መዘጋጀት ይቻላል?

እግዚአብሔርን መገናኘት የሚቻለው እራሱ እግዚአብሔር በሆነው በቅዱስ ቃሉ መሠረት በፀሎት ግንኙነት ነው። እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን ፈልገነው አላገኘነውም ብንል እራሳችንን እናስታለን። መፅሐፍ ቅዱስ በትክክል እንደሚነግረን እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን ብንፈልገው እርሱ እንደሚገኝ ነው። «እናንተ ትሹኛላችሁ በፍፁም ልባችሁም ካሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ» (ኤርሚያስ 29÷13)

ስለለብታ ሕይወት ተጠንቀቁ! እግዚአብሔርን በግማሽ ልብ፤ ዓለምን በግማሽ ልብ ማስተናገድ አይቻልም። እግዚአብሔር ድል ሊሰጠን

ይቻለዋልና በእርሱ ብቻ ተማምነን እንኑር:: (1 ቆሮንቶስ 15÷57) በመንፈስ ቅዱስም እየተሞላን ይህንን እውነት ለሌሎች እንመስክር::

## መቀበል ወይንም ያለመቀበል

ለእግዚአብሔር መሻት ሲኖራችሁ ያ መሻታችሁ እስከማይጠፋበት ጊዜ ድረስ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ:: ይህንን ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ በእምቢተኛነት ያለመቀበል ደግሞ አሳዛኝ አደጋ አለበት:: «በጽዮን ላሉ አመፀኞች ወዮላቸው» (አሞፅ 6÷1) አመፀኞች የእግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ የሚጋፉ በእግዚአብሔር ይተፋሉ (ራዕይ 3÷16)

የእግዚአብሔርን መንፈስ ለመቀበል ትህትናና ራስን ማዋረድ ያስፈልጋል (ዳንኤል 9÷3)

## በጌታ ፊት መቆየት

እህትዋ ማርታ እንዳደረገችው በልዩ ልዩ ተግባር ከመጠመድና ከጌታ ፊት ከመራቅ ይልቅ በጌታ እግር ስር የቆየችው ማርያም የተሻለ አድርጋለች:: (ሉቃስ 10÷38) የእግዚአብሔር ሃይል እርሱን በተስፋ በተጠባበቅን ቁጥር ለእኛ ይለቀቅልናል:: (ኢሳይያስ 40÷31)

እግዚአብሔርን እናገለግላለን እያልን እርሱን በተስፋ ባለመጠበቅ የምናካሂደው ሥራ ሁሉ ነገሮቻችንን ያበላሹብናል:: በህይወታችን፣ በኑሯችንና ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት መራራና የተዛባ ሲሆንብን ቆም ብለን ህይወታችንን መመርመርና በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈሱ በማረፍ መስተካከል የተገባ ጉዳይ ነው::

## ሁሉንም በፍቅር አድርጉት

አማኝ ክርስቲያኖች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆን የሚያደርጉትን ሁሉ በፍቅር ማድረግ ይገባቸዋል:: ተግሣፅም ቢሆን በፍቅር ይሁን (1 ቆሮንቶስ 16÷14) የምንሠራው ነገር ሁሉ ፍቅር ከሌለበት በንስሃ ተስተካክለን በፍቅር እንጀምረው::

## የእግዚአብሔርን ሀሣብ መከተል

«እስክመጣ ድረስ ነግዱ» (ሉቃስ 19÷13) የእግዚአብሔርን ሀሣብ በቅዱስ ቃሉ እየፈለግን የእርሱን ሥራ በትጋት መፈፀምን እንከታተል:: የሰጠን የወንጌል አደራ ታላቅ ስለሆነ ላገኘነው ሁሉ እየመሰከርን ለጌታ እናትርፍበት:: አስቀድመንም የእርሱን ጽድቅና መንግሥት እንፈልግ (ማቴዎስ 6÷33) የእግዚአብሔር መንግስት ፍቅር፣ ሰላም፣ ይቅርታና ተስፋ ነው::

**መልዕክት ከአሣታሚው**
***ሪክ ካርማይል***

# ክርስቶስን እናውጃለን

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሠጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና» (ዮሐንስ 3÷16)

በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም መንግስታትና መሪዎች ልዩ ልዩ አዋጆች ያውጃሉ:: የእግዚአብሔር መንግስት ልዩና ብቸኛ አዋጅ ደግሞ በልጁ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የዘላለም ሕይወት ሰዎች ሁሉ እንዲያገኙ መመስከር ነው::

የእግዚአብሔር ዕቅድ ዋና ዓላማ ሰዎች በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ከሰይጣን፣ ከሞትና ከፍርዱ እንዲድኑ ነው:: ሰዎችን እያሳተ በመጨረሻው ወደገሀነም የሚነዳው ሠይጣን መንግስቱ የሚፈርሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በሚገኝ እምነት በፀጋ በመኖር ነው::

«የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» (1 ዮሐንስ 3÷8) ሠይጣን ሰዎችን ለማጥፋት የሚጥር በመሆኑ ሰዎች የሚድኑበትን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳያምኑ ቢያደርግ አያስደንቅም:: (ዮሐንስ 8÷44) (1 ጴጥሮስ 5÷8) (ራዕይ 12÷9) የዚህ ዓለም ገዥ የተባለው ሠይጣን የማያምኑ ስዎችን ዓይን እንዳሳወረ ቃሉ ይናገራል:: (2 ቆሮንቶስ 4÷4)

ነገር ግን እራሱ ብርሃን የሆነው ክርስቶስ በቃሉና በመንፈሱ ያመኑትን ዓይን ከፍቷል::

ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉና በሐዋርያቱ በኩል ከሰጠን ወንጌል የተለየ ወይም የተጣመመ

የማያስተምሩ ሁሉ የተረገሙ ናቸው (ገላትያ 1÷8):: ብዙዎቹ በስም ክርስቲያን ነን ቢሉም በእምነትና በቃል የክርስቶስን ብቸኛ አዳኝነትና በስጋ መምጣቱን ዛሬም እንደሚፈወስና የስሙ ኃይል እንዳለ እስካላመኑ ድስ የክርስቶስ ወገን ሊባሉ አይችሉም:: ይልቁን የክርስቶስን የመስቀል ስራ ከካዱ የተረገሙ ናቸው::

በሚያሳዝን ሁኔታ በዛሬው ዘመን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አያሌ ጥቃትና ማሳት በዓለም ሁሉ ዙሪያ የሚደረግበት ዘመን ላይ እንገኛለን::

በሰለጠኑት በአውሮፓና በአሜሪካም ሆነ በታዳጊ የአፍሪካና የእስያ ሀገሮች ስለክርስቶስ መመስከርና በቅዱስ ቃሉ የተፃፈውን ትክክለኛ የሕይወት ኑሮ መከተልና ማስተማር በሕግ የሚያስጠይቅ እየሆነ ነው::

አያሌ ሐሰተኛ መምህራን የክርስቶስ መስቀል ሥራዎችንና ቃላትን የሚቃወሙ ሐሰተኛ ትምህርቶችን በክርስትና ስም በማስፋፋት ላይ ናቸው:: እኛ ግን ዘመን የማይሽረውን የክርስቶስን ትምህርት ለሰዎች ክፉ አስተሳሰብ ሳንገዛ እንሰብካለን፣ እንኖራለን::

«እኛም በክርስቶስ ፍፁም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሰፅን ሰውንም ሁሉ በጥበብ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱን ነው» (ቆላስያስ 1÷28) እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም ሆነ ዛሬ ለዘለአለም ያው ነው (ዕብራውያን)::

ሌሎች እንደሚሉት ክርስቶስ አልተፈጠረም፤ ፈጣሪ ነው እርሱ በስሙ ሰውን ሁሉ ያድናል እንዳስተማረውም በስሙ ፀሎት እያቀርብን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እናስተምራለን፤ እያጠመቅን ደቀመዝሙር እናደርጋለን:: (ማቴ 28÷19)

# የክርስቶስን መስቀልና ሕይወት ተካፈሉ

ማንም ሰው አዲስ ኪዳን ሲያጠና ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳለፈውን ምድራዊ ሕይወት በማገናዘብ የክርስትና ሕይወት የሚያስከትለውን አስገራሚ ልዩነት ሳይረዳ አይቀርም::

የኢየሱስ ክርስቶስን የዚህ ምድር ኑሮ በቃልና በሥራ ልንከተል ይገባናል (1 ዮሐንስ 2÷6) ጠላቶቻችንን ልንወድ ያስፈልጋል (ማቴዎስ 5÷44) ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር እንዳላቸው ሁሉ ለእኛም እንዳስተማረን ጸሎት የበደሉንን ሁሉ ይቅር ልንል ይገባናል:: በመስቀል ላይ በምስማር እጆቹ ተቸንክረው ወደታች እየተመለከተ የሰቀሉትንና አሳልፈው የሰጡትን የሮማ ወታደሮችና ፈሪሣዊያን አይሁድና ተባባሪዎቻቸውን ክርስቶስ ይቅር ብሏል:: (ሉቃስ 23÷34) (ቆላስያስ 3÷13) እኛም በእምነታችን የተነሳ ክፉኛ የሚጠሉንን ከልብ ይቅር ልንል ይገባል፤ ልንፀልይላቸውም ያሻል (ማቴዎስ 5÷44)::

ከአሸናፊዎች ሁሉ እንደምንበልጥ በቅዱስ ቃሉ በተነገረልን እውነት እንመን:: (ሮሜ 8÷37) በሁሉ ልናመሰግን ሁሉን እንድናምን ከሁሉ ጋር ተስማምተን እንድንኖር በእግዚአብሔር ቃል ታዘናል:: (ሮሜ 8÷28 ኤፌሰን 5÷20)::

በአንዳች ነገር ስንጨነቅ በምስጋናና በጸሎት ሁሉንም ለጌታ እያቀረብን አእምሮን የሚያልፈው የእግዚአብሔር ሰላም ልባችንን እንደሚጠብቅ ከጌታ ቃል ገብቶልና (ፊልጵስዮስ 4÷6) በጌታ ኢየሱስም ሁሌ ደስ ልንሰኝ ይገባል (ፊልጵስዮስ 4÷4) ያለክርስቶስ ምንም ማድረግ የማንችል ነገር ግን ከእርሱ ጋር ተካፋዮች ሠራተኞች ነን (ዮሐንስ 15÷5) (ዕብራውያን 3÷14)

የክርስቶስን መስቀልና ሕይወት መካፈል የትክክለኛ ክርስቲያን ሕይወት ባህርያት ናቸው:: በክርስቶስ በማመን ከዚህ አታላይ፣ ወረተኛ እና ዋሾ ዓለም በቃልና በተግባር መለየትና ፍቅርና ሰላምን ላለው ዘር ሁሉ መመኘትና መስጠት ክርስቶሳዊ ባህርይ ነው::

እግዚአብሔር እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ብሎ ያዘዘውን በኢየሱስ ክርስቶስና በደቀመዛሙርቱ የታየውን የተቀደሰ/የተለየ ሕይወት እኛ ክርስቲያኖች ዛሬ ልንለማመደው ይገባል:: (1 ጴጥሮስ 1÷16) ከልባችን ሞልቶ በአፋችንና በሀሳባችን ሊገለፅ የሚገባውን የክርስቶስ የሕይወት መንፈስ ሁሌ በቅዱስ ቃሉና በጸሎት ልንሞላና ለሌሎችም ልናስተላልፍ ተጠርተናል:: (ዮሐንስ 7÷38)

እራሳችንን ካልካድን የክርስቶስ መሆን እንደማንችል እራሱ ክርስቶስ ተናግሮናል (ሉቃስ 14÷26) ራስን መካድ ማለት ደግሞ እኔነትን በመጣል ክርስቶስን ማስከበርና የግል ጥቅምን በመተው ለክርስቶስ ስንል የሌሎችን ጥቅም ማክበር መንከባከብን ያጠቃልላል::

ክርስቲያኖች እንደ ነቢዩ ኢሳይያስ «ወዮልኝ» በማለት የጌታን ምህረት ለዓለም ሁሉ በማወጅ ሰዎች ከክፉ መንገድ እንዲመለሱ መምከር ይገባናል::

ክርስቶስን መስሎ መኖር በዚህ ዘመን በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ዙሪያ እጅግ አስቸጋሪ ሆኖ ቢታይም መደረግ ያለበት ብቸኛው የክርስትና አካሄድ ይህ ብቻ ነው።

# ለጌታ የመስጠት የጥሞና ሕይወት

በእውነት ከልባችሁ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ተጣብቃችኋልን? ማንም ሰው በኑሮና በሀሳብ የተጣበቀውን ነገር ወይም ሰው መምሰሉ የማይቀር ነው። እስኪ ሙሉ ልባችሁን ለጌታ መስጠታችሁን መርምሩ «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ» (ምሳሌ 23÷26) የብዙዎች የክርስትና ሕይወት ትርጉም ማጣትና ውድቀት መንስኤው ከልብ ሣይሆን ከውጭ በአፍ ብቻ ስለክርስትናቸው መመስከርና መስሎ መታየታቸው ነው። ክርስትና ግን ከውስጥ የልብ መቀየርና በውጭም፣ በኑሮና በንግግር የክርስቶስ መሆናችንን መስመስከሪያ ነው። እስኪ በየጊዜው ከጌታ የሚለየንን ኃጢያት እንርገመውና ከክፉ ሀሣብና ድርጊታችን ተለይተን በቅዱስ የእግዚአብሔርን መንፈስ በመሞላት ደግ ደጉን፣ ሰላም ያለበትን፣ ፍቅር የሆነውን እናስብና እንስራ፤ ከሰው ልብ የሰው ሕይወት ውጤት ይወጣልና፤ ልባችንን በጌታ ቅዱስ ቃልና በጸሎት እንጠብቅ (ምሣሌ 4÷23)

የእምነትና የፍቅር ኑሮ እንዲሞላብንም ፍላጐቱ ይኑረን፤ ክርስትና የቅዱስ ቃሉ ኑሮና ተግባር ስለሆነ ቅዱስ ቃሉን ማጥናት አይታክተን። «ከእርሱም ጋር ተሰቅያለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም፤ ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል። አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት ነው» (ገላትያ 1÷20) የዘወትር ጸሎታችንና መሻታችን ጌታ ሆይ ይህንን ክፉ ስጋዊና ዓለማዊ መሻቴን ስቀለው! ይሁንልን በእምነትም ጌታ ሆይ አሳድገኝ እንበለው። እምነትን በተስፋ ስለምንጠብቀው የጌታ ነገር ስለሆነ ዘወትር በተስፋ የምንመላለስ እንሁን ልባችንና ሀሣባችን በማጠፋው አታላይ ዓለም ላይ ሣይሆን በላይ በቅዱስ ጌታ ላይ ብቻ ይሁን (ቆላስያስ 3÷3)።

የኑሮ ውጣ ውረድ በበዛበት በዚህ ዘመናችን በእርጋታ ለክርስቶስ በመስጠት በጭምትነት መኖር አስቸጋሪ ሆኖብናል። ነገር ግን ሁሌም ያው የሆነው ክርስቶስን ብንማፀነው ሁሉን ያስቻላል። (ፊልጶስ 4÷13) (ዕብራውያን 13÷8)።

ለበጐ ነገር ለፍቅር ስራ እንጂ በጌታ ፊት ለመቆየት መጣደፍ የለብንም። በቀን 24 ሰዓት ለሠጠን ገታ ቢያንስ አንድ ሰዓት የጥሞና ጊዜ መስጠት ያለመቻል በጣም አሣዛኝ ጉዳይ ነው። ክርስትና ሕግና ወንጌል ስለሆነ ሕጉን በማፍረስ ፍርድ እንዳይመጣብን የክርስቶስን ወንጌልና ምህረት በእምነት እየተቀበልን ለጌታ የበለጠ በመስጠት ብንመላለስ በረከታችን የተትረፈረፈ ይሆናል።

በሰዎች ሁሉ ዘንድ ሊገለፅና ሊታይ በሚችለው በጐ እና ቅዱስ ንግግር ዘወትር እንትጋ! ይህንን እንዳንፈፅም የሚከለክለንን የሠይጣንና የስጋችንን የዚህ ዓለም ክፉ መሻትና እንቅፋት በጾምና በጸሎት እንፋለመው።

ከእኛ ጋር እስከመጨረሻው ድረስ እገኛለሁ ብሎ በቅዱስ ቃሉ ተስፋ የሠጠን ክርስቶስ የታመነ ስለሆነ ይህን እያሰብን በድፍረት በፊቱ እንትጋ (ማቴዎስ 28÷20)።

የክርስትና የጥሞና ሕይወት የየዕለት ሥራችንን ሳይነካ በምንሰራበትም ሆነ በምንጠራበት ሥፍራ ሁሉ ክርስቶስን ከልብ በመጥራት እርሱንም በቃልና በኑሮ በመመስከር ሊፈፀም የሚችል ቀላል ትዕዛዝ ነው፤ «ከእኔም ተማሩ ቀንበሬም ቀልል ሸክሜም ቀላል ነው (ማቴ 11÷29)።

# የበጉ የክርስቶስ ደም ኃይል

በዛሬው ዘመን የክርስቶስ ቅድስት ቤተክርስቲያንን የሆነውን የአማኞች ማህበረሰብ ከቅድስናውና ከመንፈሳዊ መነቃቃት ተሀድሶ የከለከለው ነገር አንድና አንድ ብቻ ያም ኃጢያት ነው።

«እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሱት» (ራዕይ 12÷11) እነማን? እነርሱ ክርስቶስን ብቻ የተማመኑ አማኞች።

ሰዎች ከእግዚአብሔር ለመለየትና በኃጢያት ለመውደቅ የምንሰጠው ምክንያት አያሌ ነው፡፡ ሥልጣኔ፣ ቤተሰብ፣ ወዳጅ፣ ዘመድ፣ ሥራ፣ ሙያ፣ ዝንባሌ፣ ማህበራዊ ኑሮ፣ ሀገር፣ ዘር፣ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ክብር፣ ዝና፣ ሕመምና ወዘተ ናቸው፡፡ ምንም ይሁን ምንም ምክንያት እንስጥ ኃጢያት ከእግዚአብሔር የሚለይ መጨረሻውም ሞትን የሚያስከትል መተላለፍ ነው፡፡ ነገር ግን የምንሰጣቸውን ሰበቦችና ምክንያቶች ቁጭ በማድረግ እንደ እግዚአብሔር ልጆች በበጉ በክርስቶስ ደም በሞቱና በትንሳኤው ኃይል የኃጢያትን ሥርና መንስኤውን ለመስበር እንነሳ፡፡

የክርስቶስ ደም በእግዚአብሔርና በሰው ዘር መካከል የነበረውን ፀብ አስወግዶ ሰላምን አስገኝቷል፡፡ (ቆላስያስ 1÷20) ዘላለማዊ ሞት በዘላለማዊ ሕይወት በክርስቶስ ደም ተቀይሯል (ዮሐንስ 6÷54) በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ኃይል ኃጢያታችሁ ዛሬ ተወግዷል/ይወገዳል (1 ዮሐንስ 1÷7) አእምሯችን ሣይቀር ከክስና ከወቀሳ በደሙ ነፅቷል (ዕብራውያን 9÷14)፡፡

የክርስቶስ መከራ፣ ሞትና ትንሳኤ በልብና ህሊናችን እስካልተሞላ ድረስ የበጉ ክርስቶስ ደም የማንፃት፣ የማዳን ኃይልን አንረዳም፡፡

እስራኤላዊያን በየዓመቱ ፍፃሜ በሚያደርጉት የጾም መስዋዕት የኃጢያት/በደል ይቅርታን ይጠይቁ የነበረ ሲሆን በመጨረሻም የበጉ የክርስቶስ ደም ተምሳሌት የሆነም ደም በመቃን/በር ላይ አየተረጨ በግብፅ ከሞት መልአክ አድኗቸዋል፡፡

በዚህም መሠረት እንደተስፋ ቃሉ የዓለምን ኃጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰጋ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ያመኑትን ሁሉ አዳነ (ዮሐንስ 1÷29)፡፡

በጉ የሚለው የክርስቶስ መጠሪያ ፍፁም ታዛዥነቱንና ትህትናውን እርሱ የሚሰጠው ትዕዛዝንም መፈፀም የሚቻል ቀላል መሆኑን ያመላክታል (ማቴዎስ 11÷29) እርሱ ፈቃዱን ለአባቱ እንዳስገዛ እኛም ፈቃዳችንን ለእርሱ ልናስገዛ የተገባ ነው፡፡ (ዮሐንስ 6÷38) ጌታ እራሱን በፈቃዱ ባዶ አድርጐ ለአባቱ በመገዛት እኛን ከሞት አድኗል (ፊልጰስዮስ 2÷8)

በትንቢት እንደተነገረለት ክርስቶስ ሁሉን እያወቀ ሁሉን ማድረግ እየቻለ በገዳዮቹ ፊት ዝም ብሎ በፈቃዱ ራሱን ለእኛ ሲል ሰዋ፤ «ተጨነቀ፣ ተሠቃየም አፉንም አልከፈተም፤ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በጠላቶቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም» (ኢሣይያስ 53÷7)፡፡

ለብዙዎች ሃይማኖተኞች ለአይሁድ ጭምር መሰናክል የሆነውና ዛሬም የማይዋጥላቸው መሲሁና የዓለም አዳኝ ጌታ በራሱ ፈቃድ ሞትን ተቀብሎ በመስቀል ላይ እንደወንጀለኛ መገደሉ ነው፡፡ ይህ መስዋዕትነት ደግሞ የክርስትና መሠረት የሆነ ለዘለአለም የማይቀር የመዳን መንገድ የሆነ የበጉ የክርስቶስ ሥራ ነው፡፡

# ክርስቶስ በእኔ ይኖራል

«እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ» (ዮሐንስ 15÷5) ብዙውን ጊዜ ክርስቶስን ከእኛ የተለየና ከእራሳችንም ውጭ ያለ አድርገነው በማሰብ ትልቅ ስህተት እንሠራለን፡፡ ነገር ግን ክርስቶስ በምሳሌው በትክክር እንደነገረን እኛና እርሱ በአንድ ዛፍ ላይ ያለን ግንድና ቅርጫፎች ነን፡፡ እርሱ ግንድ እኛ ቅርንጫፎች፡፡

ቅርንጫፎች መልካሙን ፍሬ የሚሰጡት ከግንዱ በሚያገኙት መልካም ምግብ ስለሆነ የእኛ መልካም ነገር የሚባልልን ሁሉ ከእርሱ ከክርስቶስ ከግንዱ ከተቀበልነው ነው፡፡ ክርስቶስ በገነት በሰማይ እንዳለ ሁሉ በእኔም ውስጥ እኔም ጋር እንደተስፋ ቃሉ እንደሚገኝ አምናለሁ፡፡ (ማቴዎስ 19÷20)

ክርስቶስ በየቀኑ ሕይወቴ ከእኔ ጋር ነው፡፡ ስበላና ስጠጣ፤ ከእንቅልፌ ስነሣም ሆነ ከመተኛቴ በፊት ስሙን ስጠራ ከተፍ የሚልልኝ ክርስቶስ ከእኔ ጋር ነው፡፡ «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ» አሁን እኔ አልኖርም ክርስቶስ በእኔ ይኖራል፡፡ (ገላትያ 2÷20)

ክርስቶስ በእኔ የሚኖረው በጭፍን እምነት ወይም በጉልበት ሳይሆን እንደተስፋ ቃሉ በእምነት በተስፋ አብሮኝ እንደሚኖር ቅዱስ ቃሉ ያረጋግጥልኛል፡፡ እርሱ ክርስቶስ እንደ ቃሉ በመንፈስ ከእኔ ጋር ነው፡፡ (ዮሐንስ 15 ገላትያ 2÷20) እያንዳንዳችን በራሳችን አንዳች ማድረግ የማይቻለን በክርስቶስ ብቻ መንቀሳቀስ የምንችል የክርስቶስ ንብረት ነን፡፡

ከመጀመሪያው ምድራዊ አገልግሎቱ ጀምሮ እግዚአብሔር አብ በክርስቶስ ሕይወት ተገልጿል፡፡ በእኔ ውስጥ የሚኖረው ክርስቶስ እግዚአብሔርን ያከብራል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሲወለድ የኤልሻዳይ ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ኃይል በእርሱ ላይ

ነበረ:: «አማኑኤል» እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚለው የአረማይክ ቃል ይህንን ያረጋግጣል:: አዎን ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር በአንድያ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በእኔ ይኖራል:: በእኔ ብቻ ሣይሆን በክርስቶስ አዳኝነት በሚያምኑት ዘንድ ሁሉ እስከፍፃሜው ይኖራል::

ይህንን እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ በኩል የሰጠውን ህይወት ማን ይጠብቅልናል? መልሱ እርሱ አምላክ የሆነው በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ እግዚአብሔር የሚልከው መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ በእኛ ለዘላለም እንዲኖር ሐይልና ብርታትን ይሰጠናል:: «ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አፅናኝ ይሰጣችኋል:: እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው» (ዮሐንስ 14÷16)

ዛሬ እራሳችንን ልንጠይቅ የተገባው ጥያቄ ክርስቶስ በትክክል በእኔ ይኖራል? የሚል መሆን አለበት:: በትክክል ክርስቶስ በሕይወታችን በቅዱስ ቃሉ የሚኖር ከሆነ ደግሞ ክርስቶስ የማይወዳቸው የሚፀየፋቸው የዓለም፣ የሰይጣንና የስጋ ስራዎችን የመፈለግና የማድረግ ፍላጐቱ ከእኛ ይወገዳል:: ግን እናስተውል የክርስቲያን የዚህ ዓለም ኑሮ በመንፈሳዊ ውጊያ የተሞላ ስለሆነ እንደቆራጥ የክርስቶስ ወታደር በየቀኑ ከሥጋችን ከዓለምና ከሰይጣን ጋር ላለብን ፍልሚያ እርሱን ክርስቶስንና ቅዱስ መንፈሱን ብቻ እንታመን (ኤፌሶን 6÷12)

# መላው ቤተሰባችሁ እንዲድን በእግዚአብሔር ታመኑ

«በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፤ አንተና ቤተሰዎችህም ትድናላችሁ» (ሐዋርያት 16÷31) መላው ቤተሰባችን እንዲድን የእግዚአብሔር ፈቃድና ሀሳብ ነው:: ለእግዚአብሔር ልጆች ከዚህ የበለጠ የተስፋ አፅናኝ ቃል አይኖርም:: እግዚአብሔር መንግሥተ ሰማይን በቤተሰብ ተምሳሌት ነው የመሠረተው:: «በአባቴ ቤት» (ዮሐንስ 14÷2) እግዚአብሔር በሚኖርበት ፍቅሩ መንግስቱና በረከቱ ይገኛሉ:: በሁሉም የዳነ ክርስቲያን ልብ ውስጥ ያለው ዋነኛ ነገር መንግስተ ሰማይ መኖሪያው/ቤቱ እንዴት ነው? እግዚአብሔር መንግሥቱን እንደ ቤት ማቀናጀቱ እያንዳንዱ ቤተሰብ ክርስቶስን አምኖ እንዲቀበለው በመፍቀዱ ነው::

## ኖህ

«እግዚአብሔርም ኖህን አለው አንተ ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ ወደመርከብ ግባ» (ዘፍጥረት 7÷1) የኖር መርከብ የክርስቶስ ተምሳሌት ሆኖ ከጥፋት ውሀ የኖህን ቤተሰቦችና ከየእንስሳቱ የተመረጡትን አድኗል:: በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ሁሉ ከጥፋት ውኃ ድነዋል:: የኖህ መርከብ የቤተሰቡ መዳኛ ሆኗል (ዕብራውያን 11÷7)

## አብርሃም

ጌታ አብርሃምን «የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቼንና ከእርሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝዝ አውቃለሁ» ብሎ ለቤተሰቡ በጉነት ተናግሮለታል:: እግዚአብሔር እያንዳንዱ የቤተሰብ መሪ ለቤተሰቡ ቅዱስ ትዕዛዙን እንዲያስተዳድር ሹሟል:: ሰማያዊ አባታችን የዚህ አሰራር ምሳሌያችን ነው:: እግዚአብሔር የእርሱን ቤተሰብ/መንግስቱን በፍቅር፣ በትዕግስት፣ በጥበብ፣ በፍትህና በበጐነት መምራቱ ለእኛ ለትምህርታችን ነው::

## ኤሊ

የአሁኑ ዘመን የለየለት ክፉ ጉዳይ የቤተሰብ የወላጅ ኃላፊነት መጥፋት ነው:: ይህ ጥፋት ደግሞ ከቤተሰብም አልፎ የሀገርና የመላው ዓለም ጥፋትን እያስከተለ ነው::

በካህኑ ኤሊና በልጆቹ ላይ የደረሰ የእግዚአብሔር ቁጣ በእግዚአብሔር ቤትና ቤተሰብ ላይ ኃላፊነት ተሠጥቷቸው በደልን ለሚያመጡና ክፋትን ለማይገስፁ ሁሉ በቂ ትምህርት ነው:: «ልጆቹ የእርግማን ነገር እንዳደረጉ አውቆ አልከለከላቸውምና ስለኃጢያቱ በቤቱ ለዘላለም እንድፈርድ አስታውቄዋለሁ» (1ሳሙኤል 3÷13)

ካህኑ ኤሊ ቤተሰቡንና ልጆቹን በሚገባ ባለመያዙና ባለመገሰፁ የደረሰበት ቅስፈት ዛሬ ለሁላችንም ማሳሰቢያ ይሆናል:: አንዳንዶች ልጆቻቸውን በሥርዓት ካለመያዛቸው የተነሳ ብዙ ጥፋትና አደጋ በሕብረተሰባችን ዘርን እየደረሰ ይገኛል:: በሀገራችን የታወቀው ምሳሌ እንቁላል ሰርቆ ሲያቃብላት ያልቀጣችው እናቱን በዝርፊያ ሰው ገድሎ ሊሰቀል ሲል «ምነው እናቴ በእንቁላሉ ጊዜ በቀጣሽኝ» ያላትን ያስተውሷል::

## ሊድያ

ሊድያ ብርቱና ጌታን የምትወድ ከበርቴ የንግድ ሰው ነበረች። ሐዋርያው ጳውሎስ ወንጌል ሲሰብክ ሰምታው ጌታ ልቧን የከፈተላት ስትሆን ይህንን በረከትም ከመላው ቤተሰቧ ጋር ተካፍላለች። (ሐዋርያት 16÷15)

በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን በጥንትም ሆነ በአሁኑ ዘመን እግዚአብሔር ቤተሰብን ለመንግስቱ ይጠቀማል። እኛም የእራሳችንን ቤተሰብ የክርስቶስ መገኛ ለማድረግ በቃሉና በጸሎት ስንተጋ ቤታችን መንግስተ ሰማይ ይሆናል።

# የሚሲዮናዊነት ወንጌል የማዳረስ ኃላፊነት

የቤተክርስቲያን ታሪክ እንደሚነግረን የጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የደህንነት ወንጌል ለዓለም ሁሉ እያዳረሰ ከአስራሁለት ደቀመዛሙርት/ሐዋርያት ወደቢሊዮን የደረሰው በሚሲዮናዊነት የወንጌል ማዳረስ ሥራ ነው።

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ ትዕዛዛትም ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ የእርሱን መንግስት ያመኑና የተቀበሉት እንዲያስፋፉት እንዲመሰክሩለት ነው። «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደዘመዛሙርት አድርጓቸው» (ማቴዎስ 28÷19) ስበኩ። ያመነ የተጠመቀም ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል (ማርቆስ 16÷15) «በኢየሩሳሌም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» (የሐዋርያት ሥራ 1÷8)

በእነዚህ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ትዕዛዛት መሠረት ወንጌሉ በሀገራችን ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ እስከአሁን ድረስ እየተመሰከረ እነሆ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማኞች በክርስቶስ ዳግም ተወልደው የመንግሥቱ ተሳታፊ ሆነዋል።

ይህ የክርስቶስ ወንጌል ሲመሰከርና ሲስፋፋ ግን እንደዋዛ ሣይሆን አያሌ መከራዎችና መስዋዕትነቶች በእግዚአብሔር ልጆች ላይ ደርሷል፤ ዛሬም እየደረሰባቸው ይገኛል። የጨለማው የክፋቱ መንግሥት ገዥ ሠይጣን መንግስቱ እየፈረሰ ምርኮዎቹ ወደ ክርስቶስ መንግሥት ሲገቡ ዝም ብሎ እንደማይመለከት ልናስተውል ያስፈልጋል። ሠይጣን ሲመቸው በማባባልና በማሳሳት ሳይቻለውም መሣሪያዎቹን እየተጠቀመ እውነተኛ የክርስቶስ ልጆችን ከማሣደድ አያርፍም።

እኛ የክርስቶስ ብርሀን የበራልን፤ ክርስቶስን ብቻ ጌታና አዳኝ አድርገን የምናምን ልጆቹ ዛሬም ከፍተኛ የሚሲዮናዊነት ወንጌል የማዳረስ ኃላፊነት ይጠበቅብናል። ለሥራና ለትምህርት በስደትና በመፈናቀል ወደምድራችን ኢትዮጵያ ለገቡትም ሆነ እኛ በሄድንባቸው ሁሉ ትክክለኛውን የክርስቶስ ወንጌል ልናስፋፋ፣ ልንመሠክር ተጠርተናል።

ለሚሲዮናዊ የወንጌል ማዳረስ ትልቅ ኃላፊነት በድርጅት እና በእርዳታ ብቻ መታመን አይገባንም። ከጉድለቷ ሣንቲሟን ለጌታ ቤት እንደሰጠችው ሴት ለወንጌል ቃል ማሠራጫ ከሣንቲም ጀምሮ መለገስ፣ መጸለይና በአንደበትና በሕይወት የመመስከር ኃላፊነት የሁሉም አማኝ ክርስቲያን መብት፣ ጥቅምና ግዴታ ነው። (ሉቃስ 21÷3፣ 22÷28)

አንዳንዶች በቤተሰባችንና በሥራ ቦታችን ክርስቲያን ነን ቢሉም የክርስትና መሠረት የሆነውን ክርስቶስንና ቃሉን እስካላወቁ ድረስ ከንቱ ግብዝነት ነውና እኛ ወንጌሉን ልናብራራላቸው፣ በሕይወትም ልንመሰክርላቸው ተልከናል። አንዳች ስድብ፣ ዛቻ፣ ፌዝና ስደት ቢደርስብን በዚህ በክርስቶስ ተከታዮች ሁሉ ላይ በሚደርስ ነገር ሣንሰጋ ምስክርነታችንን እንቀጥል።

# ዓለም ለቀፍ የጸሎት ዘገባዎች

## በሀይቲና ቤሉች ሥፍራዎች የተጐዱትን ለሰበ

በመሬት መናወጥ በሀይቲ በሚገኙ ሰዎች ላይ የደረሰውን መፈናቀልና ጉዳት ጌታ እንዲጠግን እንማፀነው:: በሚቻለንም በያለንበት ለተፈናቀሉትና ለታረዙት የአቅማችንን በማዋጣት በበጐ ስራ እንሳተፍ::

## ለታንዛኒያ ምልጃ እናቅርብ

በምስራቅ አፍሪካ ለምትገኘው የዛንዚባር ደሴቶችን ለምታጠቃልለው ታንዛኒያ ብርቱ ጸሎት እናድርግ:: የደሴቶቹ ሕዝቦች 99 ከመቶ ሙስሊም ሆነው አብዛኛዎቹ ሕዝቦች በመካከለኛ ው ታንዛኒያ ክርስቲያን ለሆነባት ሀገር፣ በየጊዜው ከብሩንዲና ከኮንጐ ለሚጐርፉት ስደተኞች መቋቋም እንፀልይ:: ብዙ ወላጅ አልባ ሕፃናትን ላስከተለው በዚያ የተስፋፋውን የኤድስ በሽታን ጌታ እንዲያስወግድ በብርቱ እንፀልይ::

## ለቼክ ሪፐብሊክ ወጣቶች እንፀልይ

የሚሲዮን አገልጋዮች ባቀረቡት ዘገባ መሠረት በቼክ ሪፐብሊክ የክህደት ትምህርት እንደገና በወጣቶች ዘንድ በመስፋፋት ላይ ይገኛል:: ከኮምኒዝም ውድቀት በኋላ በደህና ሁኔታ በነበረው ነፃነት የተፈጠረው የእምነት እንቅስቃሴ ፈፅሞ እንዳይቀለበስና እንዳይጠፋ በብርቱ እንማልድ::

## ምስጋና ለማረሚያ ቤቶች አገልግሎት

በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በመላው ዓለም በማረሚያ ቤቶች ለሚካሄደው የወንጌል አገልግሎት ጌታን እናመስግን:: እስራትን ሁሉ ለሚፈታ ጌታ ምልጃ ይቅረብ::

## ሕይወት የሚለውጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

በዓለም ዙሪያ የሕይወት ቃል ያለበትን የእግዚአብሔር ቃል ለማስጠናት ለሚተጉት የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበራትና አገልግሎቶች ሁሉ ለጌታ ምስጋና እናቅርብ እነዚህ ጠቃሚ አገልግሎቶችም ጸሎትና እርዳታችን አይቋረጥ::

## ጸሎት ለመካከለኛው ምሥራቅ ክርስቲያኖች

በመካከለኛው ምሥራቅ የአፍሪካ ቀንድን ጨምሮ በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው ስደትና ሰቆቃ ከዓለም እጅግ የከፋው መሆኑን ዘገባዎች ያረጋግጣሉ:: በተለይ ለክርስትና ፍፁም ተቃራኒ በሆኑት የሙስሊም ሀገሮችና እንደሶማሊያ በተመሰቃቀሉ ሥፍራዎች ወደክርስትና እምነት የሚገቡ አንገታቸው በሠይፍ የሚቀረጥ ሲሆን የሴቶችም ስቃይ እጅግ የበዛ መሆኑ ተወስቷል:: ጌታ ለእነዚህ ሕዝቦች ወንጌሉን በራሱ መንገድ እንዲያበራ እንፀልይ:: ላገኘናቸውም እንመስክር::

## ልዩ ማሳሰቢያ ለአንባቢዎች

**በየጊዜው ስለምትገልፁልን ምስጋና እና ለምትልኩልን ልባዊ ድጋፍ ጌታ የተመሰገነ ይሁን! ሁላችሁንም ከልብ እናመሰግናለን:: ለአገልግሎቱ መቀጠል ለብቸኛው መታመኛችን ለክርስቶስ በጸሎታችሁ አቅርቡን:: አቅማችሁ የፈቀደውንም በፖስታ ቤት በአድራሻችን በመላክ የወንጌል ምሥክርነታችን ተባባሪ ሁኑ::**

## የምፅዐቱ የምሥራች የወንጌል አገልግሎት


ትርጉምና ቅንብር
አደፍርስ ሀብቴ መካሻ
ሴንት ሉዊስ
አሜሪካ

አርትኦትና ዴስክቶፕ ህትመት
ኤልሣቤጥ ባስልዮስ
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ተጠሪ
አልማዝ አሣየ
የመ.ሣ.ቁ 8986
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ